699/2013

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

የፌዴራል የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ እና
የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

# የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓት ሞዴል መመሪያ ቁጥር 699/2013 ዓ.ም
## /ተሻሽሎ የቀረበ/

ግንቦት/2010 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## መግቢያ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ከግብርና ቀጥሎ ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠር የዜጎችን ገቢና የኑሮ ደረጃ በማሻሻል ድህነትን በመቀነስና የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ የማይተካ ሚና ያለው ዘርፍ በመሆኑ የዘርፉን ልማት ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስችሉ የድጋፍ ማዕቀፍ ማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤ ዘርፉን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ከሚሰጡ ድጋፎች መካከል የገበያ ትስስር ድጋፍ አንዱ ድጋፉን ተደራሽና የኪራይ ሰብሳቢነትን በር የሚዘጋ፣ ግልፅ አሰራርን የሚያሰፍን የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ የገበያ ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዘርፉ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልገውን የገበያ ትስስር ድጋፍ ከኪራይ ሰብሳቢነት የጸዳ፣ አሳታፊ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማቅረብ፣ ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረውን የገበያ ትስስር ማስፈፀሚያ መመሪያ ከአዲሱ የኤጀንሲው አደረጃጀትና ተልዕኮ አኳያ ተፈትሾ ይበልጥ ለአሰራር በሚያመች መልኩ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 14 መሠረት ይህ የገበያ ልማትና ግብይት ስርዓት ሞዴል መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

699/2013

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ልማትና ግብይት ስርዓት ለመዘርጋት የወጣ ሞዴል መመሪያ ቁጥር 699/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **"ሚኒስቴር"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ማለት ነው፡፡

2) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47/1 የተመለከቱትን ክልሎች ማለት ሲሆን ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡፡

3) **"ከተማ"** ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2 ሺህ ወይም ከዚህ በላይ የህዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አከባቢ ነው

4) **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት ቻርተር ያላቸው ከተሞችን ሳይጨምር በሌሎች ከተሞች ውስጥ እንደ ማዘጋጃ ቤት ያለ የከተማ





አስተዳደርና አገልግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመና ራሱን የቻለ አስተዳደራዊ አካል ነው፡፡

5) **"ቢሮ"** ማለት እንደየክልሉ ሁኔታ አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም በወጡት ህጎች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ስራን የሚመሩ ተቋማት ማለት ነው፡፡

6) **"ኤጀንሲ"** በፌደራል ወይም በክልል የሚገኙ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡

7) **"ገበያ"** ማለት በአካባቢ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኝና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት በተወዳዳሪ ዋጋ የሚቀርብበት ነው፡፡

8) **"የገበያ ትስስር"** ማለት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ እድል ለመፍጠር ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የአነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት (በግዢና ሽያጭ) በጎንዮሽና በተዋረድ ግንኙነት የሚፈጠርበት የገበያና ግብይት ስርዓት ነው፡፡

9) **"ጠቅላላ ካፒታል"** ማለት ህንፃን ሳይጨምር ከኢንተርፕራይዙ ጠቅላላ የቢዝነሱ ሀብት ላይ ዕዳው ተቀንሶ የሚገኘው ካፒታል ማለት ነው፡፡

10) **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር

በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

11)"**አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ**" ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን **ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 (ሃምሳ ሺህ አንድ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ)** ወይም በከተማ ግብርና፣በባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራ እና በግንባታ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ 1,500,000 (አንድ ሚልዮን አምስት መቶ ሺ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

12)"**ሞዴል ኢንተርፕራይዝ**" ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፕሮግራም ታቅፎ በራስ ጥረትና የተደረገለትን ድጋፍና ግብአት በመጠቀም ለላቀ ውጤት የበቁና በልማታዊ አመለካከቱ ለሌሎች መሰል ኢንተርፕራይዞች አርአያ በመሆን በማስፋፋት ስትራቴጂ ላይ ግንባር ቀደም የልማት ሀይል የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

13)"**የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር**" ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ ባለበት የዕድገት ደረጃ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪነቱ የቀጣይ የዕድገት ደረጃ የሽግግር መስፈርቶቹን በማሟላት የመሸጋገር ሂደት ነው፡፡

14)"**የምሥረታ/ ጀማሪ ደረጃ**" ማለት ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪግ ውጭ ያሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን





ለመመሥረት ፍላጎት ያላቸው ሰዎች እና ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት በየደረጃው የሚጠበቅባቸውን ትምህርት በማጠናቀቅና በንግድ ህጉ መሰረት ተደራጅተው የራሳቸውን ቁጠባና ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ብድር በመውሰድ ወደ ሥራ የገቡትን የሚያካትት ነው፡፡ የምሥረታ /ጀማሪ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ ሕጋዊ አቋም ይዞ የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ተግባር የሚጀምርበት ነው፡፡

15)"**የታዳጊ/ መስፋፋት ደረጃ**" ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሲሆንና ትርፋማነቱ በቀጣይነት ሲረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ያለ ኢንተርፕራይዝ በምሥረታ ደረጃ ከነበረው ቀጥሮ የሚያሠራው የሰው ኃይል ቁጥርና የጠቅላላ ሀብት መጠን ዕድገት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚጠቀም ይሆናል፡፡

16)"**የመብቃት ደረጃ**" ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የገበያ ድርሻውን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በሥራ ላይ ካዋለና ለዘርፉ የተቀመጠውን ትርጓሜ መሥፈርት ሲያሟላ ወይንም በአለበት ደረጃ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በመሆን በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን ነው፡፡

17)"**የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት**" ማለት የኢንተርፕራይዞችን ችግር የለየና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የተሟላ መረጃ ማደራጀትና

የመስጠት፣ስልጠና ድጋፍ፣ የቴክኖሎጅ ልማት፣ ግብይት፣ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍን የሚያካትት ድጋፍ ነው::

18)**"ንዑስ ተቋራጭነት"** (sub contract) ማለት የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወይም የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሥራዎችን በከፊል በመለየት ሥራውን ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመስጠት በውል የሚፈጸም የግብይት ሥርዓት ነው::

19)**"አውት ሶርሲንግ"** ማለት በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና ኩባንያዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየትና በማውጣት ሙሉ በሙሉ/ በከፊል ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርብበት የግብይት ስርዓት ነው::

20)**"ፍራንቻይዚንግ"** ማለት በተወሰኑ ለየት ባሉ ምርቶች ወይም የአገልግሎት ሂደት ውስጥ ከአምራቹ፣ ከአከፋፋዩ ወይም ከአገልግሎት ሰጪው ድርጅት ጋር የንግድ ሥምምነትና ውል በመፈጸም በውሉ መሠረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በውል ሰጪው የንግድ ስም፣ ምልክትና ፈቃድ መስራት የሚችሉበት የንግድ አሠራር ሥርአት ነው::

21)**"አውትግሮወር"** ማለት በአግሮ ፕሮሰሲንግ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጓቸውን የግብርና ግብአቶች በኢንተርፕራይዞች ተመርቶ ወይም እሴት ተጨምሮበት ከኢንዱስትሪዎች ጋር በሚደረግ ሥምምነት ውል በመፈጸም የሚቀርብበት የንግድ አሰራር ስርዓት ነው::





22)**"ኮንስትራክሽን ዘርፍ"** ማለት በሥራ ተቋራጭነት በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት፣ ባህላዊ የማዕድን ሥራዎች፣ የከበሩ ድንጋዮች ልማት፣ ጌጠኛ ድንጋይ (ኮብልስቶን) ሥራዎች፤ የመሠረተ ልማት ግንባታ ንዑስ ተቋራጭነት የሥራ ዘርፎች ማለት ነው::

23)**"የንግድ ዘርፍ"** ማለት የሀገር ውስጥ ምርቶችን በጅምላ ሽያጭ፣ በችርቻሮ ንግድና በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ላይ የሚሰራ የሥራ ዘርፍ ነው::

24)በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፣

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ሞዴል መመሪያ በኢትዮጵያ ከተሞች በሚገኙ የከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## 4. ዓላማ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቱትን ምርትና የሚሰጡትን አገልግሎት በጥራት፣ በተወዳዳሪ ዋጋና ብዛት በማቅረብ የአካባቢ፣ የክልልና አገር አቀፍ የገበያ እድሎችን በመጠቀም ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል ነው::

## 5. የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓት መርሆዎች

ለጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚደረገው የገበያ ልማትና ግብይት ድጋፍ አፈጻጸም የሚከተሉት መርሆዎች ይኖሩታል፤

1) የሚሰጡ የገበያ ድጋፎች የጠባቂነትን አመለካከት የሚያነጥፉና ኢንተርፕራይዞቹ ችግራቸውን በመለየትና መፍትሔ በማፈላለግ ሂደት ውስጥ ግንባር ቀደም የሚሆኑበት፣
2) የሚሰጡ የገበያ ድጋፎች በግልፅ መስፈርት ላይ የተመሠረቱ፣ የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረጉ፣ የተቀናጁና ተወዳዳሪነትን የሚያጎለብቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3) የአካባቢ፣ የክልልና አገር አቀፍ የገበያ ዕድሎችን አሟጦ መጠቀም፤
4) በጥራትና በዋጋ ላይ የተመሰረተ የገበያ ተወዳዳሪነትን መከተል፣
5) የንግድ አሰራርን መሠረት ያደረገና ተጠያቂነት ያለው የግብይት ሥርዓት መፍጠር፣
6) ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች ለተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው አቅም እንዲፈጥሩ ማስቻል፤
7) የመንግስት ፕሮጀክቶችን የገበያ ትስስር ድጋፍ በዋነኝነት ለጀማሪ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ መስጠት፤
8) ለሴቶች፣ለወጣቶች፣ለአካል ጉዳተኞችና ለስደት ተመላሾች እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ምሩቃን ቅድሚያ መስጠት





# ክፍል ሁለት

## የገበያ ዕድሎች፣ ትስስር አማራጮችና የግብይት ሥርዓት

### 6. የአካባቢ ገበያዎች

ከተሞች የግብይት ማዕከላት እንዲሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የምርትና የአገልግሎት አቅራቢዎች በመሆንና ከአካባቢው አርሶ አደሮች የግብርና ምርት ጥሬ ዕቃዎችን እንዲጠቀሙ በማድረግ በከተማና በገጠር መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር በከተሞች አካባቢ ያለውን የገበያ ዕድል አሟጠው መጠቀም እንዲችሉ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን አለባቸው።

1) በከተሞችና በገጠር አካባቢዎች ያሉ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ የአካባቢ የገበያ ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና በገበያ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

ሀ) በከተሞች የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊጠቀሙበት የሚችሉ የገበያ ዕድሎችን ከተለያዩ የንግድና የዘርፍ ማህበራት፣ ከዘርፍ ማህበራት ህብረቶች ጋር በመቀናጀት ወይም ባለሙያዎችን በመጠቀም በዝርዝር መለየት

ለ) የተለዩ የገበያ ዕድሎችን በመጠን፣ በዓይነት፣ በጥራት ደረጃ በዝርዝር በመለየትና በማደራጀት መረጃው ለኢንተርፕራይዞቹ እንዲደርሳቸው ማድረግ ፤

ሐ) በአካባቢ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ኢንተርፕራይዞች በአቅርቦት፣ በዋጋና በጥራት በብቃት ተወዳዳሪ ሆነው ማቅረብ እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ዓይነት

መለየትና በሁሉም የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግ፤

መ) በአካባቢ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ኢንተርፕራይዞች በአቅርቦት፣ በዋጋና በጥራት በብቃት ተወዳዳሪ ሆነው ማቅረብ እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን የፋይናንስ ድጋፍ ዓይነትና መጠን በመለየት በሁሉም የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማመቻቸት፤

ሠ) የተለዩ የአካባቢ የገበያ ዕድሎች ስፋት ያላቸው ከሆኑ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው በጋራ የገበያ ዕድሉን እንዲጠቀሙ ማስቻል፤

2) በአካባቢ ባሉ የገበያ ዕድሎች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በዋጋ፣ በጥራት፣ በአቅርቦት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ የምርታማነትና ጥራት ማሻሻል፣ የወጪ ስሌትና የዋጋ ትመና አቅም ለማሳደግ የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት፤

ሀ) የተለዩ የአካባቢ የገበያ ዕድሎች ከዋጋ አንፃር ያለውን ውድድር በዝርዝር እንዲተነተን በማድረግ የዋጋው ሁኔታ ከአቅርቦት ጋር የሚኖረውን ለውጥና ኢንተርፕራይዞቹ ሊያገኙት የሚችሉትን የትርፍ መጠን ማስላት፤

ለ) የተለዩ የአካባቢ የገበያ ዕድሎችን ጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መጠቀም እንዲችሉ በገበያ ውስጥ በአቅርቦትና በዋጋ ተወዳዳሪ በመሆን፣ ወጪ ቆጣቢ የሆኑና ምርታማነታቸውን የሚያሳድግ አሠራሮችን በሥራ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ በአነስተኛ ዋጋ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤





ሐ) የተለዩ የአካባቢ የገበያ ዕድሎችን ኢንተርፕራይዞች መጠቀም እንዲችሉ በገበያ ውስጥ በጥራት ተወዳዳሪ መሆን ይኖርባቸዋል፤ ስለሆነም የሚያመርቱት የምርት ስታንዳርድና የሚጠቀሙበት የጥሬ ዕቃና የሚገለግሉባቸው መሣሪያዎች ዓይነት አጠቃቀም የመለየት ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ፤

3) የጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአካባቢው ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ምርትና አገልግሎታቸውን ማቅረብ እንዲችሉ የተለያዩ የሽያጭ ስልቶችን እንዲጠቀሙ ድጋፍ ማድረግ፤

ሀ) ለጅምላ ሽያጮች፣

ለ) በሽያጭ ስራ ላይ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በማስረከብ

ሐ) ለሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር ሱቆች ምርቶቻቸውን በማስረከብ

መ) በንግድ ትርኢትና ባዛር በመሳተፍ፣

ሠ) በመንግስት ተቋማት እና በግል ድርጅቶች በሚወጡ ጨረታዎች በመሳተፍ፣

ረ) ለተለያዩ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ምርትና አገልግሎት አቅርቦት የዱቤ ሽያጭ በማካሄድ፣

ሰ) ከመንግስት ተቋማት እና ከግል ድርጅቶች ጋር የንዑስ ተቋራጭነት ሥራ በማከናወን፣

4) የአካባቢ ጥሬ ዕቃን መሠረት ያደረጉና ተወዳዳሪነትን የሚያረጋግጡ ምርቶችን እሴት ሰንሰለትን ማዕከል በማድረግ የምርት ልማት በማከናወን በአካባቢ ተፈላጊ የሆኑ ምርትና አገልግሎቶችን በማቅረብ ታዋቂነትና ተቀባይነት እንዲያገኙ ማድረግ፤

ሀ) በአካባቢው በስፋት የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን እሴት የሚጨመርባቸውን በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ማከናወን፤

ለ) በተጠናው የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የኢንተርፕራይዞችንና የባለድርሻ አካላትን ሚና ለይቶ ማስቀመጥ፤

ሐ) በአካባቢው የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችንና የገበያ ዕድልን ከግምት በማስገባት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በስፋት እሴት የመጨመር ሥራ ውስጥ እንዲገቡ የሚያስፈልጋቸውን የድጋፍ ዓይነት መለየትና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤

መ) በአካባቢው በስፋት የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች የመልማት ዕድልና ከሌሎች ተመሳሳይ ጥሬ ዕቃዎች አንፃር ያላቸውን ብልጫ በዝርዝር ማመላከትና እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፤

ሠ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለምርቶቻቸው የጥራት ደረጃ መመዘኛ እንዲያሟሉ በማድረግ በአካባቢው፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ በንግድ ትርኢቶችና በሌሎች የማስተዋወቂያ ስልቶች ሰፊ የማስተዋወቅ ስራ መስራት፤

5) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች በከተሞች በሚደራጁ የገበያ ማዕከላት እንዲሸጡ ማድረግ፤

ሀ) በአካባቢው ገበያ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊቀርቡ የሚችሉ የምርት ዓይነቶችን በእሴት ሰንሰለት ጥናት መሠረት በዝርዝር መለየት፤

ለ) የገበያ ማዕከላትን በየከተሞቹ በብዛት ማዘጋጀትና ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

ሐ) የገበያ ማዕከላቱ በአካባቢው፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ታዋቂነት እንዲኖራቸው በገበያ ማዕከላቱ የሚቀርቡ ምርቶችን





ዓይነት በመዘርዘር በተለያዩ ዘዴዎች በማስተዋወቅ ተጠቃሚዎች እንዲለምዷቸው ማድረግና ተጨማሪ የገበያ ዕድልን መፍጠር፤

6) ከሌሎች አካባቢዎችና ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችንና በአካባቢው የሚመረቱትን በዝርዝር በመለየት በኢንተርፕራይዞች ሊመረቱ የሚችሉትን ምርቶች ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና የአካባቢውን ህብረተሰብ ግንዛቤ በማሳደግ የገበያ ዕድሎችን በመፍጠር በጥራት፣ በዋጋና በአቅርቦት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤

ሀ) ከሌሎች አካባቢዎችና ከውጭ ሀገር በስፋት ወደ አካባቢው ገበያ የሚገቡ ምርቶችን ዝርዝር በማወቅ በኢንተርፕራይዞች ሊመረቱ የሚችሉትን በመለየትና የተለዩ ምርቶችን ዓይነት በየዘርፉ በማደራጀት ዝርዝር መረጃን መያዝ፣

ለ) በተገኘው ዝርዝር መረጃ መሠረት በአካባቢው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶቹን ለማምረት የሚያስፈልጋቸውን የክህሎት፣ የመሣሪያ፣ የፋይናንስና ሌሎች አቅርቦቶችን ማመቻቸት፣

ሐ) ከሌሎች አካባቢዎችና ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተመሳሳይ መልኩ ከሚመረቱት ምርቶች ጋር በማወዳደር በጥራት፣ በዋጋና በአቅርቦት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣

መ) በኢንተርፕራይዞች የተመረቱት ምርቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ከውጭ ሀገርና ከሌሎች አካባቢዎች ከሚገቡ ምርቶች ጋር በማነፃፀር ተወዳዳሪ መሆናቸውን

በማመላከት ህብረተሰቡ ምርቶችን እንዲጠቀም ማነሳሳትና ማበረታታት፣

## 7. የክልል ገበያዎች

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በከተሞች የገበያ ተወዳዳሪነታቸው ሲረጋገጥ የገበያ አድማሳቸው የሰፋ ይሆናል፡፡ ይህም ከአካባቢ ገበያ ባሻገር በክልል ውስጥ ምርትና አገልግሎታቸውን ለማቅረብ የሚያስችላቸው አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ በክልል ውስጥ ያሉ የገበያ ዕድሎችን ለመጠቀም እንዲችሉ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

1) በክልል ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ የገበያ ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና በገበያ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

ሀ) በክልል ደረጃ በገበያ የሚፈለጉና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊቀርቡ የሚችሉ የምርት ዓይነቶችን በመለየት መረጃዎችን በየደረጃው ማስተላለፍ፤

ለ) በክልል የተለዩትን የገበያ ዕድሎች በመጠን፣ በዓይነት፣ በጥራት ደረጃ በዝርዝር በመለየትና በማደራጀት ምርቶችን ሊያመርቱ ለሚችሉ ኢንተርፕራይዞች መረጃው እንዲደርሳቸው ማድረግ፤

ሐ) በክልል ገበያ ውስጥ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪ ሆነው ምርቶቻቸውን ማቅረብ እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤





መ) በክልል ገበያ ውስጥ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪ ሆነው ምርቶቻቸውን ማቅረብ እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን የፋይናንስ ድጋፍ ማመቻቸት፤

ሠ) የተለዩ የክልል ሰፋፊ የገበያ ዕድሎችን ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው በጋራ እንዲጠቀሙ ማስቻል፤

2) በክልል ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ጥሬ ዕቃን መሠረት ያደረጉና በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የማይገኙ ምርትና አገልግሎቶችን በመለየት ከሚመረቱባቸው ከተሞች ባሻገር በክልሉ ውስጥ ባሉ የተለያዩ አካባቢዎች ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎታቸውን ማቅረብ እንዲችሉ የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት፤

ሀ) በክልሉ ውስጥ በየአካባቢዎቹ የእሴት ሰንሰለትን መሰረት በማድረግ የተለዩትን በስፋት የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን እሴት የሚጨመርባቸውን በመለየት ማደራጀትና በክልሉ ውስጥ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በጥሬ ዕቃዎቹ እንዲጠቀሙ ማስቻል፣

ለ) በክልል ገበያ ጥሬ ዕቃዎቹን እሴት በመጨመር ምርትን ሊያመርቱ የሚችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የማምረት አቅም ዝርዝር መረጃ በማደራጀት በጋራ ለክልል ገበያ ኢንተርፕራይዞች ተቀናጅተው ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያቀርቡ መደገፍ፣

ሐ) ከተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ተጠቅመው በክልል ገበያ ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያቀርቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን

የሚያስፈልጋቸውን የድጋፍ ዓይነት መለየትና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤

3) በአንድ ከተማ ታዋቂነት ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶች በክልሉ ሌሎች ከተሞች በስፋት እንዲሸጡ ለኢንተርፕራይዞች የሽያጭ እድል እንዲያገኙ ድጋፍ መስጠት፤

ሀ) ከየከተሞች ለክልል ገበያ ሊቀርቡ የሚችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርቶችን በመለየት ከጅምላ ሻጮችና ከሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራት ሱቆች ጋር ማስተሳሰር፤

ለ) በየከተሞች ታዋቂነትን ያገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ክልሉ በሚያዘጋጀው የንግድ ትርኢትና ባዛር ላይ እንዲሳተፉና የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ሁኔታዎች ማመቻቸት፤

ሐ) በክልል ደረጃ የሚወጡ ጨረታዎችን መረጃ በማደራጀትና በማሰራጨት በከተሞች የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ ማድረግ፤

መ) በክልል ደረጃ በሚወጡ ጨረታዎች ላይ የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ስለ ጨረታ ሰነድ ዝግጅት፣ የዋጋ አሞላልና የአቅርቦት ሁኔታ በቂ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እንዲገኙ ማድረግ፤

ሠ) በክልል ደረጃ በተለያዩ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ለሚገኙ ሠራተኞች ስለ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ያላቸውን ዕውቀትና ግንዛቤ በማሳደግ ከኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶችን በዱቤ እንዲገዙ ማድረግ፤





4) በክልሉ የተለያዩ ከተሞች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ሀገር ከሚመጡ ምርቶች በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት በማነፃፀር ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሐን በቋሚነት የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት፤

ሀ) በክልሉ ውስጥ በስፋት ከውጭ ሀገር የሚገቡና ጥቅም ላይ የሚውሉ ምርቶችን ዝርዝር በማወቅ በኢንተርፕራይዞች ሊመረቱ የሚችሉትን መለየት፤

ለ) በክልሉ በስፋት ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን ዓይነት በየዘርፉ በማደራጀት ዝርዝር መረጃን መያዝ፤

ሐ) በተገኘው ዝርዝር መረጃ መሠረት በክልሉ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርቶቹን ለማምረት የሚያስፈልጋቸውን የክህሎት፣ የመሣሪያ፣ የፋይናንስና ሌሎች አቅርቦቶችን ማመቻቸት፤

መ) ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን በክልሉ በሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በተመሳሳይ መልኩ ከሚመረቱት ምርቶች ጋር በማወዳደር በጥራት፣ በዋጋና በአቅርቦት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤

ሠ) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተመረቱት ምርቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ከውጭ ሀገር ምርቶች ጋር በማነፃፀር ተወዳዳሪ መሆናቸውን በማመላከት በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን ህብረተሰብ ምርቶችን እንዲጠቀም በክልሉ መገናኛ ብዙሐን የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፤

በትምህርት ቤቶች፣ በገበያ አካባቢዎችና በክልል ውስጥ በሚዘጋጁ መድረኮች ማስተዋወቅ፤

5) በከተሞች የገበያ ዕድልን በመፍጠር ረገድ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በክልል ደረጃ የማስፋት ተግባራትን ማከናወን፤

ሀ) የገበያ ዕድል በመጠቀም ምርጥ ተሞክሮ ለመቀመር የሚያስችሉ የአፈፃፀም መመዘኛዎችን በጥንቃቄ መለየት፤

ለ) በመመዘኛው መሠረት ከየከተሞቹ የተሻለ የገበያ ዕድል መጠቀም የቻሉ ኢንተርፕራይዞችን መለየት፣

ሐ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ዕድልን ለመጠቀምና ለውጤታቸው ምንጭ የሆኑትን አሠራሮች መለየት፤

መ) የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች መቀመርና በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ኢንተርፕራይዞችና አስፈፃሚ አካላት እንዲጠቀሙበት በተለያዩ ስልቶች ማስፋት፤

## 8. የሀገር አቀፍ ገበያ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በክልል ደረጃ ምርትና አገልግሎታቸውን በተወዳዳሪነት ማቅረብ መቻላቸው በቀላሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የገበያ አማራጮችን ለመጠቀም ያስችላቸዋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚኖሩ የገበያ ዕድሎች ስፋት ያላቸው በመሆናቸውና ስብጥራቸውም የበዛ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎታቸውን በተደራጀ አግባብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የገበያ





ዕድሎችን ለመጠቀም እንዲችሉ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል።

1) በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የገበያ ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች መረጃውን እንዲያገኙና በገበያ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

ሀ) በሀገር አቀፍ ደረጃ በገበያ የሚፈለጉና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊቀርቡ የሚችሉ የምርት ዓይነቶችን በመለየት መረጃዎችን በየደረጃው ማስተላለፍ፤

ለ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለዩትን የገበያ ዕድሎች በመጠን፣ በዓይነት፣ በጥራት ደረጃ በዝርዝር በመለየትና በማደራጀት መረጃው ለክልሎች እንዲደርሳቸው ማድረግ፤

ሐ) በየክልሉ ያለውን የገበያ ዕድል ወጥነት ባለው የመረጃ ሥርዓት እንዲያደራጁ ድጋፍ መስጠት

መ) የገበያ ዕድሎችን የመለየት አቅማቸውን ለማሳደግ የሚያስችል ሥልጠና መስጠት፤

ሠ) በተለያዩ ክልሎች ያሉ የገበያ ዕድሎችን ዝርዝር መረጃዎች በማደራጀት በየክልሉ ለሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊደርስ የሚችልበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

2) በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት ወደ ሀገር ውስጥ እየገቡ ያሉ ምርቶችን ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራት፣ ደረጃ፣ ዋጋ በዝርዝር በመለየት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተወዳዳሪነት እንዲያመርቱ ለማድረግ የተሟላ የመረጃ አገልግሎትና የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት፤

ሀ) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን ዓይነት፣መጠን፣ጥራት፣ ደረጃና ዋጋ መረጃዎችን በየዘርፉ በማደራጀት ማሰራጨት፤

ለ) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን መነሻ በማድረግ በኢንተርፕራይዞች ሊመረቱ የሚችሉትን መለየት፣

ሐ) ምርቶቹን ለማምረት የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂና የክህሎት ግብአቶችን በዝርዝር መተንተንና ለኢንተርፕራይዞች የሚደርስበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

3) በየክልሉ የገበያ ዕድልን በመፍጠር ረገድ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በሀገር አቀፍ ደረጃ የማስፋት ተግባራትን ማከናወን፤

ሀ) የገበያ ዕድል በመጠቀም ምርጥ ተሞክሮ ለመቀመር የሚያስችሉ የአፈፃፀም መመዘኛዎችን በጥንቃቄ መለየት፤

ለ) በመመዘኛው መሠረት ከየክልሎቹ የተሻለ የገበያ ዕድል መጠቀም የቻሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን መለየት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዞቹ የገበያ ዕድልን ለመጠቀምና ለውጤታቸው ምንጭ የሆኑትን አሠራሮች መለየት፤

መ) የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች መቀመርና በሁሉም ክልሎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በተለያዩ ስልቶች ማስፋት፤

4) ኢንተርፕራይዞቹ የሚያቀርቧቸው ምርትና አገልግሎቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲያገኙ ከውጭ ሀገር ከሚገቡ ምርቶች ጋር በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት በማነፃፀር ተወዳዳሪ መሆናቸውን በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲሰርፅ በማድረግ ሰፊ የገበያ ዕድል መፍጠር፤





## 9. የገበያ ዕድሎችን ማስፈፀሚያ ስልቶች

ከላይ በተራ ቁጥር 2.1 ሥር የተጠቀሱትን የአካባቢ፣ የክልልና የሀገር አቀፍ የገበያ ዕድሎች ውጤታማ በሆነ መልኩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መጠቀም እንዲችሉ የሚከተሉት ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

1) በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በአካባቢ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የገበያ ዕድሎችን ዝርዝር መረጃ የያዘና በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የገበያ መረጃ ሥርዓት ከአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ጀምሮ በየደረጃው እስከ ፌደራል ኤጀንሲው ድረስ እንዲደራጅ ማድረግ።

2) የሀገር ውስጥ ወቅታዊ የሆኑና ገበያው የሚጠይቀውን የምርትና የአገልግሎቶች ስታንዳርድ ዲዛይንና ፓተርኖች ለኢንተርፕራይዞች የሚሠራጭበት አሠራር መዘርጋት፤

3) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርት የሚተዋወቅበት የካታሎግ፣ የድረ-ገጽና የሕትመት ስታንዳርዶች የሚዘጋጁበት አሠራር መዘርጋት፤

4) የኢንተርፕራይዞች ምርት በቋሚነት የሚተዋወቅበት የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከላት በከተሞች፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጀበትን ሥርዓት መቅረጽ፤

5) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶችና አገልግሎቶች በንግድ ትርኢቶችና ባዛሮች የሚተዋወቅበትን ዝርዝር አሠራር መቅረጽ፤

6) ኢንተርፕራይዞችን የጅምላ ግዥና ሽያጭ ለማከናወን የሚያስችል አቅም መፍጠር፤

7) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እርስ በርሳቸው ፣ ከአነስተኛ ፣ ከመካከለኛና ከፍተኛ ኩባንያዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው የሚያደርግ የድጋፍ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ፤

8) የፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የሀገር ውስጥ ገበያ በማፈላለግና ከሀገር ውስጥ የቴክኖሎጂና የዘርፍ ድጋፍ ሰጪ ኢንስቲትዩቶች ጋር በመቀናጀት ኢንተርፕራይዞች በራሳቸው ተደራጅተው የጅምላ ግዥና ሽያጭ የሚያከናውኑበትን አሠራር መዘርጋት፤

9) ኢንተርፕራይዞች በራሳቸው በዘላቂነት ገበያን እንዲያፈላልጉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤

10)የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙበትን አሠራር መዘርጋት፤

11)የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ደረጃውን የጠበቀ የሽያጭና ግዥ ውሎች ከደንበኛው ጋር ለመፈፀምና ለመጠቀም የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ፤

12)የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶችና አገልግሎቶች የገበያ ዕድልን የመለየት ሥራ እሴት ሰንሰለት መሠረት አድርጎ እንዲከናወን ማድረግ፤

## 10. የገበያ ትስስር የሚፈጠርባቸው የግብይት ዓይነቶች

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከአነስተኛ፣ ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተለያዩ መንገዶች የሚፈጥሯቸው የገበያ ትስስሮች ኢንተርፕራይዞቹ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶችን በጥራት፣በዋጋና በአቅርቦት ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ





እንዲያቀርቡ አቅም የሚፈጥርላቸውና የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ከዚህ የገበያ ትስስር ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ሊሆን ይገባል። የገበያ ትስስር የሚፈጠርባቸው የግብይት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

### 1) የንዑስ ተቋራጭነት የገበያ ድጋፍ የሚፈጠርላቸው ኢንተርፕራይዞች

በንዑስ ተቋራጭነት የግብይት ሥርዓት የሚሳተፉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሲሆኑ የድጋፉ ተጠቃሚ የሚሆኑት በማኑፋክቸሪንግና በኮንስትራክሽን የስራ ዘርፍ የተሰማሩ መሆን ይኖርባቸዋል። የንዑስ ተቋራጭነት የግብይት ሥርዓት በሚከተሉት አግባቦች ይፈፀማል፤

**ሀ) ከመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ማለትም፦** የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ግንባታ፣በባቡር መንገድ ግንባታ፤በስኳር ልማት ፕሮጀክቶች/ፋብሪካ ግንባታ፣ ቤቶች ግንባታና መስኖ ልማት/፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ፣ የመንገድ ፕሮጀክቶች፤ የቴሌኮሙኒኬሽን የግንባታ ፕሮጀክቶች፤ የኤሌክትሪክ ኃይል የመስመር ዝርጋታ ፕሮጀክቶች፤ የቤቶች ልማት ዘርፍ (የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ)፣አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎችና ነባር ዩኒቨርሲቲ ማስፋፊያ፤ የኮብል ስቶንና ሌሎች የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች፤ ውኃና ኢነርጂ ዘርፎች ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ይፈጠራል፤ በንዑስ ተቋራጭነት የግብይት ሥርዓት ከላይ የተመለከቱት የመንግስት ፕሮጀክቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ሊከናወኑ የሚችሉ ሥራዎች

በዝርዝር እንዲለዩ በማድረግና በፕሮጀክቶቹ አስፈፃሚ ተቋማት የጋራ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ኢንተርፕራይዞቹ በንዑስ ተቋራጭነት የግብይት ሥርዓት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ መሰረት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከመካከለኛና ከፍተኛ ተቋራጮች ጋር የንዑስ ተቋራጭነት እንዲሰሩና እንዲበረታቱ ይደረጋል ተብሎ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከተቋራጮች ጋር ከሚደረጉ የግንባታ ስራዎች ውስጥ 40% የሚሆነው ስራ በንዑስ ተቋራጭነት ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ከተቋራጮች ለኢንተርፕራይዞች በንኡስ ተቋራጭነት የሚሰጡ ስራዎች የህንጻ ግንባታ፣ ቀለም ቅብ፣ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ ልስን ስራ፣ጅፕሰም ስራ፣ የወለል ንጣፍ ስራ፣ የሳኒተሪ ስራዎች፣ቴራዞ ንጣፍ፣ መስኮትና በር የመሳሰሉትን የሚያካትት ሲሆን ብሎኬት፣የፕሪካስት ቢም፣ጠጠር እና ሌሎች ግብዓቶችን ተቋራጮች ከኢንተርፕራይዞች እንዲገዙ በማድረግ ትስስሩን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

ለ) ከግልና ከመንግስት አነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ከመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች፡- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በግልና በየደረጃው ከሚገነቡ የመንግስት ተቋማት ግንባታ፣ ከአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ጋር የሚኖራቸው የንዑስ ተቋራጭነት የገበያ ትስስር ሁለቱንም አካላት ተጠቃሚ ባደረገ መልኩ ሊተገበር ይገባል፡፡ በንዑስ



ተቋራጭነት የገበያ ትስስር በዋነኛነት ከጨርቃጨርቅና ጋርመንት ኢንዱስትሪዎች ጋር በሽመና፣ በልብስ ስፌት፣በማሽነሪ ጥገና፣ ሥራ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ጋር፣ በቆዳና በቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች ጋር ጫማና ሌሎች የቆዳ ውጤቶች ሥራ የተሰማሩ፣ ኢንተርፕራይዞች የጫማዉን ወይም የጃኬትን ወይም የቦርሳን ከፊል ክፍል እንዲያምር በማድረግ፣ ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች (የብየዳ ኢንጀነሪንግ፣ የበርና መስኮት ሥራ፣የማሽነሪ ጥገና) ምሳ መስፍን ኢንዱስትሪያል /እና ቢሾፍቱ አዉቶሞቲቭ እና ከአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች (በጥሬ ዕቃዎች ላይ ከፊል እሴት መጨመር፣ፓኬጂን ሥራ) ሊተገበር ይችላል፡፡

ሐ) የዘርፍ ኢንስቲትዮቶችም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ሰፊ የውጭ የገበያ ዕድል በማመቻቸት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በንዑስ ተቋራጭነት እንዲሰሩ በተለየ ሁኔታ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

### 2) የአውት ሶርሲንግ የግብይት ሥርዓት

መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች፣ የግል ኢንተርፕራይዞች፣ ማዘጋጃ ቤቶች (አገልግሎቶች ጽ/ቤቶች) የማኑፋክቸሪንግ ስራዎችን፣ የውሃና የመብራት ቢል የመሰብሰብ ሥራዎችን፣ የምግብ ግብዓቶች አቅርቦት፣ የጽዳት ሥራዎችን፣ የጥበቃና የመሳሰሉትን ሥራዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በቀጥታ በአውትሶርስ ውል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሰሩ የሚደረግበት የግብይት ስርዓት ነው፡፡

በማኑፋክቸሪንግ፣ በኮንስትራክሽንና በአገልግሎቶች ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የሚከተሉት የገበያ ትስስር ይሰጣል::

ሀ) **በእንጨትና ብረታብረት የስራ መስክ** የተሰማሩ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ከቤቶች ልማት፣ ከቴሌና መብራት፣ ከውሃና ፍሳሽ እንዲሁም ከትምህርት ተቋማት የውስጥ ጥገና ሥራዎችን (የዴስክ፣ ጠረጴዛና ሌሎች ሥራዎችን) ፣ ከግብርና ልማት ቢሮዎች (ዘመናዊ የውሃ መሳቢያ ፓምፖችን፣ የንብ ቀፎዎችን የእርሻ መሳሪያዎችን) የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንዲቀርቡ ማድረግ፤

ለ) **በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት** ለተሰማሩ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ከሀገር ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ከትምህርት ቤቶች (ዩኒፎርም)፣ ከመንግስት መ/ቤቶች (የደንብ ልብሶች ስፌት፣ ለመጋረጃና መሰል የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ውጤቶች)፤ የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንዲቀርብ ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ጋር የተያያዙ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፎች መስጠት፤

ሐ) **በደረቅ ምግብ ወይም የባልትና ውጤቶች** ለተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሆስፒታሎች፣ ከማረሚያ ቤቶች፣ ከሌጆችና ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከትልልቅ ሆቴሎችና ሌሎች ድርጅቶች ጋር የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንዲቀርብ ከደረቅ ምግብ ዝግጅት ጋር የተያያዙ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፎች መስጠት፤



የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓት ሞዴል መመሪያ

መ) **በኮንስትራክሽን ዘርፍ** ለተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕርራይዞች በጀማሪ፣ በታዳጊና በመብቃት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ሙሉ በሙሉ በአውትሶርሲንግ የገበያ ትስስር ሊከናወኑ የሚችሉ የግንባታ ሥራዎች በመለየት በኢንተርፕራይዞቹ እንዲከናወኑ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ መስጠት፤

ረ) **በአገልግሎት ዘርፍ** ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከማዘጋጃ ቤቶች (አገልግሎቶች ጽ/ቤቶች) የደረቅና ቆሻሻ ማሰባሰብ ሥራዎችን፣ የቀልዝ ስራዎችን፣ የአነስተኛ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን፣ የከተማ ውበትና መናፈሻ፣ ዘላቂ ማረፊያ ማስዋብ፣ የመንገድ ጽዳት ሥራዎችን፣ የከተማ ውስጥ የማስታወቂያና ቢልቦርድ ሥራዎችን ፣ የጥበቃ አገልግሎት፣ የውሃና መብራት ቢል፣ የኪራይ ቤቶችን የወርሃዊ ኪራይ የመሰብሰብ ሥራዎችን የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ በኢንተርፕራይዞች እንዲከናወኑ ድጋፍ መስጠት፣ በየደረጃው የሚገኙ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ጽ/ቤት ከእያንዳንዱ መንግስታዊ ተቋም አውትሶርስ መደረግ ያለበትን ሥራ በመለየት ከተቋማቱ ጋር በመነጋገር የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ የገበያ ትስስር መፍጠር ይጠበቅበታል::

ሰ) ከላይ ከ1-5 በተጠቀሱት የአውትሶርሲንግ የግብይት ሥርዓቶች ከመንግስት ፕሮጀክቶች ጋር የሚፈጠሩ የገበያ ትስስሮች ሲሆኑ ቀጣይነት ባለው መልኩ በተለያዩ ደረጃ ባሉ የግል ኢንተርፕራይዞች ብዛት ያላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች በአውትሶርሲንግ የግብይት ሥርዓት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል:: በመሆኑም በዋነኛነት ኢንተርፕራይዞች ትስስሩን

በራሳቸው የሚፈጥሩ ሆኖ በየደረጃው ያሉ በተለይ የከተማ የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች በዚህ ዘርፍ ያሉ የአውትሶርሲንግ የገበያ ትስስር ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት ኢንተርፕራይዞቹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

## 3) የፍራንቻይዚንግ የግብይት ሥርዓት

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በፍራንቻይዚንግ የግብይት ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ) ኢንተርፕራይዞች የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የንግድ ምልክታቸውን፣ የንግድ ፈቃዳቸውን፣ የንግድ ስማቸውን፣ የምርት ስታንዳርዳቸውን በመጠቀም ምርቶችን እንዲያመርቱና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ፣ እንዲያከፋፍሉ ወይም በኮሚሽን ለመሸጥ እንዲችሉ እንደየእድገት ደረጃቸው በክልል ወይም በፌደራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በኩል የገበያ ትስስር እንዲመቻች ይደረጋል።

ለ) በፍራንቻይዚንግ የግብይት ሥርዓት የሚተሳሰሩ ኢንተርፕራይዞች በሚቀበሉት የምርትና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚጠበቅባቸውን የሙያና የሥራ ልምድን ጨምሮ ሌሎች በፍራንቻይዘሩ ድርጅት የሚቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል።

ሐ) የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ምልክት፣ የንግድ ሥም፣ የንግድ ፈቃድና ሌሎች የቴክኖሎጂ ስልጠናዎችን





ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመስጠት በፍራንቻይዚንግ የግብይት ስርዓት ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

መ) በፍራንቻይዚንግ የግብይት ሥርዓት መሠረት ውል ሰጪና ውል ተቀባይ በውል ስምምነት ወቅት የፍራንቻይዚንግ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በሚሰጠው የንግድ ስራ ያሉ የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቶችና ዝርዝር ሁኔታዎች የሁለቱን ወገኖች ሙሉ መረጃና ፍላጎት ያካተተ መሆኑን አውቆ በጥንቃቄና በግልጽ መደራደር ይኖርባቸዋል፣ ሁለቱ ወገኖች በውል ተቀባይ ስለሚሰራው አገልግሎት በጋራ የቢዝነስ ፕላን (የገበያ እቅድ) ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣ የፍራንቻይዚንግ አገልግሎት በተመለከተ ሊኖሩ የሚችሉ ማንኛውም ክፍያዎችን በግልጽ በውል ስምምነቱ ላይ መካተታቸውንና ግልጽ ያልሆነ ክፍያ አለመኖሩን በጋራ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፣ የውል ተቀባይ የመነሻ ካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች በሙሉ በግልጽ መታወቅ ይኖርባቸዋል፣ ውል ተቀባይ አገልግሎቱን በሚሰጥበት ወሰን ውስጥ ከውል ሰጪ ምርትና አገልግሎት ውጪ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ድርጅት ውል ተቀብሎ መስራት አለመቻሉን በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፣ ውል ተቀባይ ፍራንቻይዝ ያደረገውን አገልግሎት የመስሪያ መሳሪያዎች ቀላል ጥገናዎች በውል ሰጪው በሚዘጋጅለት ማኑዋል መሠረት ጥገናውን በራሱ ማከናወን ይኖርበታል።

ሠ) **የፍራንቻይዝ ውል ሰጪ መብቶች፡-** የንግድ ምልክቱና አርማዉ ይጠበቁለታል፣ የንግድ ሥራ ሃሳቡ ይጠበቁለታል፣ የአመራረት ስልቱና እውቀቱ ይጠበቁለታል፣ የምርቱ ጥራትና ደረጃ

ይጠበቅለታል፤ የንግድ ምልክቱና አርማው በግልጽ ቦታ ይቀመጣል፤የውል ሰጪው በመረጠው ቀለምና የንግድ ምልክት የታተመበ የደንብ ልብስ የዉል ተቀባይ ሰራተኞች ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ የንግድ ምልክት የመቀየር የማሻሻል የስምምነት አካል የማድረግ መብት፤ በስምምነቱ መሰረት ምርቱ/አገልግሎቱ የንግድ ምልክቱ በትክክለኛዉ መንገድ፤ በታማኝነት እንዲተዋወቅለት የማድረግ መብት አለዉ ከዉል ተቀባዩ የንግድ ምልክት፤ የምልክት /የንግድ ስም/የንግድ ፍቃድ መጠቀሚያ ክፍያ የመቀበል መብት

ረ) **የውል ሰጪ ግዴታዎች :-** በቢዝነስ ፕላን መሠረት በውል ተቀባዩ የገበያ ሽፋን ክልል ውስጥ ውል ሰጪ ተመሳሳይ ምርት ወይም አገልግሎት ለ3ኛ ወገን የፍራንቻይዝ ፈቃድ ያለመስጠት፤ በውል ተቀባይ የገበያ ሽፋን ክልል ውስጥ በተመሳሳይ ወይም በፍራንቻይዘሩ የንግድ ምልክት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ እንዳይጠቀሙ መከላከል ይኖርበታል፤ ለአገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ የአሰራርና የቴክኒክ ስልጠናዎችን መስጠት ይኖርበታል፤ በስምምነቱ መሰረት የንግድ ፍቃዱን የንግድ ምልክቱን እንዲጠቀሙበት መፍቀድና ዋስትና መስጠት ይኖርበታል ዉል ተቀባዩን በመስረታዉ ሂደትና በሚጠቀምበት ጊዜ የመደገፍ ግዴታ አለበት

ሰ) **የውል ተቀባይ መብቶች:-** በቢዝነስ ፕላን መሠረት በእሱ የገበያ ሽፋን ክልል ውስጥ ለሌላ ወይም ለ3ኛ ወገን ሳይሰጥ ለብቻው የመስራት መብት፤ ለአገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ የአሰራርና





የቴክኒክ ስልጠናዎችን ከፍራንቻይዘሩ የመጠየቅ እና በስምምነቱ መሰረት የዉል ሰጭዉን የንግድ ምልክት/ስም/ፍቃድ የመጠቀም መብት አለዉ::

ሸ) **የውል ተቀባይ ግዴታዎች:-** የውል ሰጪን የንግድ ሥራ ሃሳብ፣የአመራረት ስልትና እውቀት የመጠበቅ፤የምርቱን ጥራትና ደረጃ የመጠበቅ፤የንግድ ምልክቱንና አርማውን በግልጽ ቦታ የማስተዋወቅ፤የውል ተቀባይ ሰራተኞች የውል ሰጪው በመረጠው ቀለም፣ የንግድ ምልክትና የታተመበ የደንብ ልብስ የመጠቀም፤በውል ስምምነቱ ላይ የተቀመጠውን ክፍያ የመፈጸም፣ ሌሎች በውሉ ስምምነቱ የተቀመጡ ግዴታዎችን የመፈጸም፤ ለሚጠቀምበት የንግድ ምልክት/ስም/ፍቃድ ለዉል ሰጭዉ በስምምነቱ የተገለፀዉን ክፍያ የመፈፀም፤ የንግድ ምልክት/ስም/ፍቃድ ከምስረታዉ ጀምሮ በስምምነቱ በተገለፀዉ ቦታ/አካባቢ የመጠቀም ግዴታ ይኖርበታል::

4) **የአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት**

ሀ) የግብርና ውጤቶች የሆኑ በከፊል የማዘጋጀት፤ እሴት በመጨመር ለአነስተኛ፣ ለመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚያቀርቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት እንዲተሳሰሩ ይደረጋል::

ለ) በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት ሊከናወኑ የሚችሉ ዝርዝር ሥራዎችን በመለየት ከመካከለኛና ከፍተኛ የአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች የማስተሳሰር ሥራዎች ያከናውናሉ::

ሐ) በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን የአቅርቦት አቅም ለማሳደግ እንዲቻል በኢንተርፕራይዞች ህብረት ወይም በሌላ ሕጋዊ አደረጃጀት ተደራጅተው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

መ) በአወትግሮወር የግብይት ሥርዓት ምርቶቻቸውን ለመካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ለሚያቀርቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢንዱስትሪዎቹ የሚፈልጉትን የምርት ዓይነትና ደረጃ እንዲያሟሉ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጣቸው ሲሆን በተጨማሪም ከክልሉ የግብርና ቢሮ ወይም የግብርና ምርምር ተቋም ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ይሰጣቸዋል::

ሠ) የግብርና ምርቶች በማቀነባበር (የአግሮ ፕሮሰሲንግ) ሥራ ላይ የተሰማሩ መካከለኛና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጋቸውን በከፊል እሴት የተጨመረበት የግብርና ጥሬ እቃዎችን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲቀርብላቸው የተቀናጀ ድጋፍ ይደረግላቸዋል::

ረ) በአውትግሮወር የግብይት ስርዓት ሊሰሩ ከሚችሉት አንዱ በአዋሽ አግሮ ኢንዱስትሪ በአግሮፕሮሰሲንግ ለሚመረቱ ምርቶች ግብዓት የሚሆኑ የፍራፍሬ ምርቶችን ኢንተርፕራይዞች እንዲያመርቱ በማድረግ ትስስር መፍጠር ይቻላል::

ሰ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከመካከለኛና ከፍተኛ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ጋር በሚያደርጉት የአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት እሴት ሰንሰለትን መሠረት በማድረግ እንዲከናወን የእያንዳንዱ ተዋንያን ድርሻ በዝርዝር





እንዲለይ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን መወጣት እንዲችሉ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል::

ሸ) በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት እሴት ሰንሰለት መሠረት በማድረግ በዝርዝር እንዲለዩ ይደረጋል::

ቀ) የግብርና ጥሬ ዕቃ አምራቾችና በከፊል እሴት የሚጨምሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመካከለኛና ከፍተኛ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች በሚሰጥዋቸው የምርት ዲዛይን፣ ጥራት፣ ስታንዳርድና መስፈርት መሠረት እንዲያመርቱ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣቸዋል::

በ) በክልሉ ውስጥ በአውትግሮውር የግብይት ሥርዓት ሊከናወኑ የሚቻልባቸውን የግብርና ምርቶችን ዝርዝርና የሚገኙባቸውን ቦታዎች ከክልሉና በየደረጃው ካሉ የግብርና ቢሮዎችና የግብርና ምርምር ተቋሞች ጋር የክልሉ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋሉ::

ተ) በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት የሚሳተፉ ተዋንያን ሕጋዊ አደረጃጀት፣ የግብይት ውል አፈፃፀም፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በተመለከተ ዝርዝር አሠራር እንዲኖረው ይደረጋል::

ቸ) ስለግብይት ውል አፈጻጸም በየደረጃው የሚፈጠረው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ከመንግስት ተቋማትና ከውጪ ኩባንያዎች ጋር በሚፈጠረው የገበያ ትስስር የውል አፈጻጸም በሀገሪቱ የንግድ ሕጎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል::

## ክፍል ሶስት

## የእድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ የገበያ የድጋፍ ፍላጎትና የሚሰጡ ድጋፎች

### 11. የኢንተርፕራይዞች የገበያ ድጋፍ ፍላጎት በዕድገት ደረጃ

1) በጀማሪ/ምስረታ ደረጃ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጋቸው የገበያ ድጋፍ በዚህ የእድገት ደረጃ ላይ ኢንተርፕራይዞች ለገበያ አዲስ በመሆናቸው የሚገጥማቸው የገበያ ተግዳሮቶች ቀላል አይደለም:: ስለሆነም የገበያ ውድድሩን እንዲለማመዱና ቋሚ ደንበኞችን እንዲያፈሩ ከመንግስት የልማት ድርጅቶችም ሆነ ከአነስተኛ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር እንደዚሁም ከነባርና ከበቁ ኢንተርፕራይዞች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ መደገፍ በጣም አስፈላጊ ነው:: በአካባቢው፣ በክልሉና በሀገሪቱ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ዝርዝር መረጃ፣ የንግድ ስራ አመራር ስልጠና፣ የመሸጫ ቦታ ድጋፍ፣ ምርትና አገልግሎትን በአካባቢው ገበያ ማስተዋወቅ የሚችሉበት ኤግዚቢሽኖች፣ንግድ ትርዒቶችና ባዛሮች እንዲዘጋጁና የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ይፈልጋሉ::

2) በታዳጊ /መስፋፋት ደረጃ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጋቸው የገበያ ድጋፍ በታዳጊ ደረጃ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ውስጥ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል እና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ:: የንግድ ስራ አመራር ስልጠና፣ የመሸጫ ቦታ ድጋፍ፣ ምርትና አገልግሎትን በአካባቢና በክልል ገበያ





ማስተዋወቅ የሚችሉበት ኤግዚቢሽኖች፣ ንግድ ትርዒቶችና ባዛሮች እንዲዘጋጁላቸው እና ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ይፈልጋሉ::

3) በመብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጋቸው የገበያ ድጋፍ ፍላጎት የገበያ ድርሻን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎች፣ ከአካባቢና ከክልል ገበያ በተጨማሪ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢንተርፕራይዙ ምርቶች በኤግዚቢሽኖች፣ ንግድ ትርዒቶችና ባዛሮች፣ በካታሎግ፣ በድረ ገፅ እና በተለያዩ ሚዲያዎች እንዲተዋወቁ በማድረግ የገበያ እድሎች እንዲሰፉ ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠር፣ ሰፊ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚፈለጉ ምርቶች ዓይነት፣ ብዛትና ጥራት ወቅታዊ መረጃ፣ ኢንተርፕራይዙ በሀገር አቀፍ ደረጃ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪነቱ እንዲጎለብት የሚያስችል ድጋፍ እንዲደረግላቸው ይፈልጋሉ::

## 12. የእድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ የገበያ ድጋፍ አሰጣጥ

### 1) ከኤግዚቢሽንና ባዛር፣ ከምርት ማሳያና መሸጫ ሱቆች /ኢምፖሪየም/ ድጋፍ አንጻር

የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሰረት በማድረግ በየደረጃው የሚገኙ የዘርፉ ፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላት በሚያዘጋጁት የተለያዩ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲሁም በምርት ማሳያና መሸጫ ሱቆችን በመጠቀም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየአካባቢዉ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ የአካባቢ የገበያ ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት በአካባቢ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የገበያ እድሎችን በመለየትና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አሠራሮችን በሥራ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራቱን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ እና ምርታማነታቸውን የሚያሳድግ አሠራሮችን በሥራ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ የገበያ ትስስር ይፈጠራል፡፡ ስለሆነም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየእድገት ደረጃቸው በተለያዩ ገበያዎች በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች እና ባዛሮች እንዲሁም የምርት ማሳያ እና መሸጫ ሱቆች የሚኖራቸውን ተሳትፎ በአካባቢ ገበያ በጥቃቅን ጀማሪ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰፊውን ድርሻ የሚይዙ ሲሆን፣ የክልል ገበያ በጥቃቅን ታዳጊ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞችን በአብዛኛው የሚያሳትፍና በጥቃቅን መብቃት የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙትን በተወሰነ መልኩ እንዲሳተፉ ሲደረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ገበያ በጥቃቅን ታዳጊና መብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙትን በብዛት የሚያሳትፍ ይሆናል፡፡ በገበያ ዕድሎች እንደየ እድገት ደረጃቸዉ የኢንተርፕራይዞች ተሳትፎ ከዚህ በታች





በተቀመጠው ሰንጠረዥ የተመለከተ ስለሆነ በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡

**ሰንጠረዥ** 1.የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ የሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየእድገት ደረጃቸው በተለያዩ ገበያዎች በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች እና ባዛሮች እንዲሁም የምርት ማሳያ እና መሸጫ ሱቆች የሚኖራቸውን የተሳትፎ ድርሻ በመቶኛ የሚያሳይ ሲሆን ከጠቅላላ ተሳታፊዎች 50% በሴቶች፣75% በወጣቶች እና 3% በአካል ጉዳተኞች የሚመሩ ኢንተርፕራይዞች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

| ተ.ቁ. | የገበያ ድጋፍ ዓይነት | ጥቃቅን | | | ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ የሚገኙ አነስተኛ አንተርፕራይዞች. | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጀማሪ | ታዳጊ | የበቁ | ጀማሪ | ታዳጊ | የበቁ |
| 1 | **የኤግዚቢሽን እና ባዛር ተሳትፎ** | | | | | | |
| 1.1 | የአካባቢ | 53 | 29 | 10 | 5 | 2 | 1 |
| 1.2 | የክልል | | 54 | 32 | 7 | 5 | 2 |
| 1.3 | ሀገር አቀፍ | | 40 | 49 | 2 | 3 | 6 |
| 2 | **የምርት ማሳያና መሸጫ (ኢምፖሪየም)** | | | | | | |
| 2.1 | ፌደራል | | 38 | 59 | 1 | 1 | 1 |
| 2.2 | ክልል | 3 | 56 | 32 | 4 | 3 | 2 |

2) ከመንግስት ግዥ አፈጻጸም አንጻር የሚደረጉ ድጋፎች

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመንግስት የእቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ በተቀመጠው ልዩ አስተያየት መሰረት የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው መደገፍ ያስፈልጋል::

**ሰንጠረዥ 2. በየእድገት ደረጃው እና በየዘርፍ ሊፈጠር የሚገባ የገበያ ትስስር መጠን በብር**

| የኢንተርፕራይዙ ዓይነት | የእድገት ደረጃ | ሊሳተፉበት የሚገባ የጨረታ ወይም የኮንትራት ስራ በብር በዘርፍ | |
|---|---|---|---|
| | | ኢንዱስትሪ | አገልግሎት |
| ጥቃቅን | ጀማሪ | እስከ ብር 600,000.00 | እስከ ብር 200,000.00 |
| | ታዳጊ | ከብር 600,001.00 እስከ 2,500,000 | ከብር 200,001.00 እስከ 1,000,000.00 |
| | የበቁ | ከብር 2,500,001 እስከ 5,000,000 | ከብር 1,000,001.00 እስከ 2,000,000.00 |
| ከማኑፋክቸሪግ ውጪ የሚገኙ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (በከተማ ግብርና በባህላዊ ማዕድን ማምረት እና በግንባታ ዘርፍ ) | ጀማሪ | ከብር 5000,001.00 እስከ 6,500,000 | ከብር 2,000,001.00 እስከ 2,500,000.00 |
| | ታዳጊ | ከብር 6,500,001 እስከ 8,000,000 | ከብር 2,500,001.00 እስከ 3,000,000.00 |
| | የበቁ | ከብር 8,000,001.00 እስከ 10,000,000.00 | ከብር 3,000,001.00 እስከ 4,000,000.00 |





በዚህ ሰንጠረዥ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በአንድ ጊዜ ሊሰጥ የሚችለው የገበያ ድጋፍ ሲሆን በተለያየ ጊዜ የሚሰጠው የገበያ ድጋፍ በኢንዱስትሪው ዘርፍ በሁለት ዙር የተገኘው አጠቃላይ ሽያጭ ብር 19,000,000.00 /አስራ ዘጠኝ ሚልዮን ብር/ እስካልሞላ ድረስ ከተመሣሣይ አንቀሳቃሾች ጋር የመወዳደር መብቱ የተጠበቀ ነው:: ሆኖም ብር 19,000,000.00 /አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር ከሞላ ለሌሎቹ እድል ለመስጠት ሲባል በዚህ ልዩ መብት ተጠቃሚ አይሆንም:: በአገልግሎት ዘርፍ በሁለት ዙር የተገኘው አጠቃላይ ሽያጭ ብር 8,000,000.00 /ስምንት ሚልዮን ብር/ እስካልሞላ ድረስ ከተመሣሣይ አንቀሳቃሾች ጋር የመወዳደር መብቱ የተጠበቀ ነው:: ሆኖም ብር 8,000,000.00 /ስምንት ሚልዮን ብር/ ከሞላ ለሌሎቹ እድል ለመስጠት ሲባል በዚህ ልዩ መብት ተጠቃሚ አይሆንም::

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በ2008 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችሉ አንቀፆች እንዲካተቱ ተደርጓል:: በዚህም መሠረት፤

3) ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የገበያ ድጋፍ የግብይት ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የባለ በጀትም ሆነ የልማት ድርጅት በበጀት ዓመቱ ከሚፈጽማቸው የሀገር ውስጥ ምርቶች ግዢዎች ውስጥ በክልሉ የግዥ መመሪያ መሠረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል::
4) ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶች የግዥ ፍላጎት ሲኖረው:-

ሀ) በከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወይም ጽ/ቤት በኩል የምርት አቅራቢ ኢንተርፕራይዞች ጥሪ ተደርጎላቸው የተጠየቀውን ምርት/አገልግሎት ማቅረብ መቻላቸው ሲረጋገጥ የኢንተርፕራይዙ ዝርዝር መረጃ በጽሑፍ ለግዥ ፈጻሚው መ/ቤት መላክ ይኖርበታል::

ለ) የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በጨረታ ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞች ዋጋን መሰረት ያደረገ በጨረታ አግባብ አሸናፊውን በመለየት ግዢውን በውል ይፈጽማል::

ሐ) ማንኛውም መስሪያ ቤት ለኢንተርፕራይዞች የፈጠረውን የገበያ ትስስር በብር መጠን የተፈጠረላቸውን ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር በየሩብ ዓመቱ ለኤጀንሲው (ጽ/ቤት) ማሳወቅ ይኖርበታል::

መ) በንዑስ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 4) (ሐ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ፈጻሚው የጨረታ ሂደቱ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በመንግስት የጨረታ መመሪያ መሠረት ጨረታውን ውድቅ በማድረግ ሌላ ዙር ጥሪ ማድረግ ይችላል::

5) በፌደራል መስሪያ ቤቶች የሚኖረውን የምርትና አገልግሎት ግዥ አስመልክቶ የሚከተለው ተግባራዊ ይደረጋል::

ሀ) በዩኒቨርሲቲዎች የምርትና የአገልግሎት ግዢዎች ውስጥ የምግብ ግብዓት አቅርቦቶች (የእንጀራ፣ዳቦ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጽዳት ሠራተኞች የደንብ ልብስና ሌሎች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መቅረብ የሚችሉ ግብዓቶችን በአካባቢው ከተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በማወዳደር የተሻለውን በመምረጥ



የገበያ ትስስር በተናጠል ወይም በጋራ እንዲያቀርቡለት የገበያ ትስስር ይፈጥራል::

ለ) የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን፣ የፌዶራል የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የፌዶራል ትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በተለይም የስኳር ልማት ኮርፖሬሽን በክልሎች በከተማና በገጠር የሚሰሩ ሥራዎችን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊሰሩ የሚችሉትን በመለየት ለኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ይፈጥራል::

ሐ) በኢንተርፕራይዞች ሊሰሩ የሚችሉ የኮንስትራክሽንና ሌሎች ሥራዎችን በመለየት በአካባቢው ለተደራጁ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችና ከማኑፋክቸሪንግ ውጪ የሚገኙ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ይሰጣል::

6) ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች ከተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመንግስት መ/ቤቶች በሚፈጽሟቸው ግዥዎች በጨረታ ሲወዳደሩ ከሌሎች ተጫራቾች በተለየ ሁኔታ የሚከተሉት ድጋፎች ይደረግላቸዋል::

ሀ) ለጨረታ የተዘጋጀውን ሰነድ በነፃ እንዲወስዱ ይደረጋል::

ለ) በጨረታ ማስከበሪያ፣ የውል ማስከበሪያና በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱን ከአደራጃቸው አካል በሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል::

ሐ) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው በጨረታ ውድድር ላይ ሲሳተፉ የሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች

እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች የጥራት ደረጃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድረው ካገኙት ነጥብ ላይ ለኢንተርራይዞቹ በተጨማሪ የሚሰጠው ነጥብ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡፡ በዚህ አግባብ ተሰልቶም ነጥባቸው ከሌሎች ጋር እኩል ከሆነ ቅድሚያ ለእነዚህ ኢንተርፕራይዞች እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

መ) የቅድመ ክፍያ ለማግኘት ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ከአሸነፉበት ጠቅላላ ዋጋ ለዕቃዎች፣ ለአገልግሎቶችና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ስራዎች በመንግስት የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት እንዲከፈላቸው ይደረጋል፡፡

7) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከ2ኛ ወገን የሚያደርጉትን የሥራ ውል መሠረት በማድረግ የብድር ዋስትና ፈንድን ግዴታ በማሟላት ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

8) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ እጥረታቸውን ለማቃለል የሥራ ማስኬጃ ብድር በሚወስዱበት ጊዜ የመንግስት የግዥ ፈላጊ ድርጅቶች፣ በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትና በኢንተርፕራይዙ/ዞቹ በሶስትዮሽ ውል ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

9) ከመንግስት ግዥ አቅራቢነት የሚያሰርዙ ጥፋቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ) በቂ ምክንያት ሳይኖር በውል መሠረት ዕቃና አገልግሎት አለማቅረብ፣





ለ) ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ያልጠበቀ ዕቃና አገልግሎት ማቅረብ፣

ሐ) በልዩ አስተያየት ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በውል ያልተካተቱ ተጨማሪ ሁኔታዎችን መጠየቅ፣

መ) በመንግስት በኩል የሚደረጉ ድጋፎችን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ መሆኑ በበቂ መረጃ ሲረጋገጥ፣

ሠ) ያለ በቂ ምክንያት ጨረታውን ካሸነፈ በኋላ ሥራውን የተወ ወይም የሥራውን ቅድመ ክፍያ ወስዶ ሥራውን ያቋረጠ ኢንተርፕራይዝ ለተከታታይ ሶስት ጨረታዎች እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤ ላስከተለውም ኪሳራ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ረ) ሆን ተብሎ የጨረታ ስርዓቱን ለማዛባት እንዲሁም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ከጨረታ ተወዳዳሪዎች ጋር ዋጋ ተስማምቶ ዝቅተኛ ዋጋ ለማቅረብ መሞከሩ በየደረጃው ባሉ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ጽ/ቤት ሲረጋገጥ ለተከታታይ ሶስት ጨረታዎች እንዳይሳተፍ ማገድ፡፡

## 13. በኢንተርፕራይዙ በራሱ የገበያ እድሎችን ከመጠቀም አንጻር

የዘርፉን ልማት ለማፋጠን በሁሉም የእድገት ደረጃ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች በየደረጃው በሚገኙ ፈጻሚ አካላት የሚሰጡ የገበያ ድጋፎች የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ ድጋፍ ለመስጠት በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት በአካባቢ፣ በክልል እና በሀገር አቀፍ ደረጃ

የሚገኙ የገበያ እድሎችን ኢንተርፕራይዞች እንዲጠቀሙ ለማድረግና የሚሰጡ የገበያ ድጋፎች የጠባቂነትን አመለካከት የሚያነጥፉና ኢንርተርፕራይዞቹ ችግራቸውን በመለየትና መፍትሔ በማፈላላግ ሂደት ውስጥ ግንባር ቀደም የሚሆኑበት እድል መፍጠርና በራሳቸው ጥረት የገበያ እድሎችን አሟጠው ከመጠቀም አንጻር የሚኖራቸውን ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1) በጀማሪ ደረጃ በኮንስትራክሽን ንኡስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ 30% በላይ፣ በብረታብረትና የእንጨት ንኡስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ50% በላይ፣ በተቀሩት ንኡስ ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ70% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን ይኖርበታል፡፡
2) በታዳጊ ደረጃ በኮንስትራክሽን ንኡስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ35% በላይ፣ በብረታብረትና የእንጨት ንኡስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ60% በላይ፣ በተቀሩት ንኡስ ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ70% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን ይኖርበታል፡፡
3) በመብቃት ደረጃ ላይ በየትኛውም ዘርፍና ንኡስ ዘርፍ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች 70% በራሳቸው የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ የሚደረግ ሲሆን 30% በመንግስት ድጋፍ የገበያ ትስስር እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 14. የጥሬ እቃ አቅርቦትን ማመቻቸት

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸውን የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ





ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በየክልሎቹ መዘጋጀቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ የጥሬ እቃ አቅርቦትን በተመለከተ የሚከተሉት አሰራሮች በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1) በየዘርፉ ለተደራጁ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ የሆኑ የጥሬ እቃ

ዓይነቶች መረጃ ተሰብስቦ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የመረጃ ቋት እንዲገባ ይደረጋል፤ መረጃውም የሚከተሉትን ዋና ዋና ዝርዝሮች ያካተተ ይሆናል፡፡

ሀ) የጥሬ እቃው ዓይነትና መጠን፣

ለ) ጥሬ እቃው የሚገኝበት አካባቢ/ቦታ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ወይም ከውጪ የሚገባስለመሆኑ፣

ሐ) የጥሬ እቃው የዋጋ ዝርዝር በአካባቢው ዋጋ መሠረት (ከውጪ የሚገባ ከሆነ በአሜሪካን ዶላር (መጠን ይገለጻል)፣

መ) ጥሬ እቃውን ወደ ማምረቻ ቦታ ለማድረስ የሚጠይቀው የትራንስፖርት ዓይነት የሚፈጀው የወጪ መጠን፣

ሠ) ጥሬ እቃው በግልጽ የተለየ የጥራት ደረጃ እና የወጪና ገቢ የንግድ ሕጎችን ማሟላት የሚጠበቅበት መሆን ወይም አለመሆኑ፣

ረ) ጥሬ ዕቃውን ለመግዛት የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ዋጋ፣

ሰ) ሌሎች ከጥሬ እቃዎችጋር የተያያዙ መረጃዎች

2) በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የተሰበሰበውን መረጃ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የእያንዳንዱን ጥሬ

እቃ ዋጋና ዝርዝር ሁኔታዎች፣ ጥሬ ዕቃውን ለሚፈልጉ ኢንተርፕራይዞች በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ባለሙያ በኩል በማሳወቅ በጋራ ግዢ እንዲፈጽሙ የማመቻቸት ሥራ ይከናወናል::

3) በክላስተር ውስጥ ተመሳሳይ ምርት አምራች ኢንተርፕራይዞች ጥሬ ዕቃዎችን በጋራ እንዲገዙና ጥሬ እቃው ከሚገኝበት ቦታ ወደ ማምረቻ ቦታቸው ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለማጓጓዝ የጋራ ኮሚቴ ያቋቁማሉ:: በእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ ፍላጎት መሰረት ግዥ የሚፈጸም ሆኖ ጥሬ እቃውን በወሰዱት መጠን በኢንተርፕራይዙ ስም ደረሰኝ የሚቆረጥ ይሆናል::

4) የተመረጠው ኮሚቴ ጥሬ እቃውን ከገዢው ሂደት እስከ ማምረቻ ቦታ ለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ በአግባቡ እንዲከፋፈል ያደርጋል::

5) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የተጠቀሰው የጋራ ግዢ ሂደት እንደተጠበቀ ሆኖ በክላስተር ማዕከላቱ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በጋራ ጥሬ እቃዎችን መግዛትና ማጓጓዝ የማይችሉ ከሆነ የሚከተሉት አማራጮች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሥራ ላይ ይውላሉ::

ሀ) በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን ከአቅራቢዎች በጅምላ ገዝተው በክላስተር ማዕከላት ለሚሰሩ ኢንተርፕራይዞች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያከፋፈሉ የጥሬ እቃ አቅራቢ ኢንተርፕራይዞች በማህበር ተደራጅተው ለክላስተሩ አባላት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርቡ ይደረጋል::





ለ) ከውጪ የሚገቡና ከፍተኛ መጠን/ብዛት ያላቸው የጥሬ እቃዎች አቅራቢዎች ጋር በማገናኘት ጥሬ እቃ አቅርቦት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

ሐ) ከላይ በሀ እና ለ የተጠቀሱት ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የጥሬ እቃ አቅርቦት በመንግስት የልማት ድርጅቶችም ሊቀርቡ ይችላሉ::

## 15. ምርትና አገልግሎትን የማስተዋወቅ ሥርዓት

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶች /አገልግሎቶች/ ለሕብረተሰቡና ለተጠቃሚው በተለያዩ የማስተዋወቂያ ዘዴዎች በየደረጃው በሚገኙ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወይም ጽ/ቤት አማካይነት ተግባራዊ ይደረጋል:: የኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎታቸውን የሚተዋወቁባቸው ዘዴዎች የሚከተሉት ሲሆኑ እነሱም፦

1) **ኤግዚቢሽንና ባዛር** ማለት በየደረጃው የሚገኙ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ጽ/ቤት በራሳቸውና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በመፍጠር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቱትን ምርትና አገልግሎት የሚያስተዋውቁበት፣ ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት፣ ኢንተርፕራይዞች የወደፊት ደንበኞችን በአካል በማግኘት፣ በመወያየትና ፍላጎታቸውን በመለየት የምርት ማሻሻያዎች ማድረግ የሚችሉበት እና የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበት ስልት ነው::

2) **በምርት ማሳያና መሸጫ ሱቅ /ኢምፖሪዩም/** ማለት የሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርቶች በመረከብ ለእይታ የሚቀርብበት፣ የሚተዋወቅበትና የሚሸጥበት ሱቅ ማለት ነው:: ዝርዝር አሰራሩ በምርት ማሳያና መሸጫ ሱቅ/ኢምፖሪያም የአሰራር ማኑዋል መሰረት ይፈፀማል::

3) **የቅዳሜ፣ እሁድና የበዓላት ቀን ገበያ:-** በተወሰነ የከተማ ክልል ውስጥ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በአላትን ምክንያት በማድረግ በተወሰነ ሰዓት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት አማራጭ መንገዶችን በማዘጋጀትና በዋና አደባባይ ላይ ያሉ መንገዶች ላይ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ይዘው እንዲገበያዩ ደረጋል:: ዝርዝር አሰራሩ የቅዳሜ፣ እሁድና የበዓላት ቀን ገበያ የአሰራር ማኑዋል መሰረት ይፈፀማል::

4) **የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ሱቆች:-** በህብረት ስራ ማህበር አዋጅ አማካኝነት በተደራጀና መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎችን ለአካባቢው ህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በሚያቀርቡ ሱቆች ዉስጥ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች እንዲገባ በማድረግ የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት ማለት ነው:: ዝርዝር አፈጻጸሙ ከፌደራል የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ጋር በሚደረግ የጋራ ስምምነት ሰነድ ይፈጸማል::





5) **ድህረ-ገጽ**

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አጠቃላይ ዝርዝር ፕሮፋይል በድህረ- ገጽ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሁም በክልሎች የሥራ ቋንቋ በሚከተሉት አካላት ይዘጋጃል::

ለ) በፌዴራል የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከሁሉም ክልሎች ጋር ትስስር ያለው ድህረ-ገጽ የሚዘጋጅ ሆኖ ድህረ-ገጹ ዘርፉን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ መረጃዎች፣ ተሞክሮዎች፣ አሠራሮች በዝርዝር የያዘና ተጠቃሚዎች ወዲያውኑ ግብረ-መልስ የሚያገኙበት ስርዓት ይዘረጋል::

ሐ) በሥራ ላይ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ በሚያመላክት መልኩ በየክልሉ የከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች ድህረ-ገጽ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል::

መ) በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚዘጋጁ ድህረ-ገጾች በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የገበያ ዕድሎችና የተለያዩ ጨረታዎች፣ የምርትና አገልግሎት ዋጋዎች፣ የጥራት ደረጃዎች ወቅታዊ በሆነ መልኩ አደራጅቶ ይይዛል::

ሠ). የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ድህረ-ገጹን በመጠቀም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያና ሌሎች መረጃዎች እንዲሰጡና መረጃውን በመጠቀም እንዲደግፉ ይደረጋል::

6) **በዳይሬክተሪና ካታሎግ**

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶችን ዓይነትን፣ ዲዛይንን፣ ስፔስፊኬሽንና አቅርቦትን በፎቶ ግራፍ በተደገፈ አግባብ ደረጃውን የጠበቀ ካታሎግ በማዘጋጀት ለኢንተርፕራይዞች ምርት ገዥዎች እንዲሰራጭና እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

ለ) በየዓመቱ በወረዳዎች፣ በክልሎች፣ በከተሞችና በፌዴራል ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን ለሕብረተሰቡ የገበያ ትስስር ለሚፈጥሩ አካላት ዳይሬክተሪ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችና የመንግስት ተቋማት እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡

7) ቢዝነስ ካርድ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ቢዝነስ ካርዶችን በዝቅተኛ ዋጋ በማሳተም ለበርካታ ተጠቃሚዎች ማሰራጨት ይችላሉ፡፡ ቢዝነስ ካርድ የኢንተርፕራይዙን ስምና አድራሻ እንዲሁም ስለሚመረተው ምርትና ስለሚሰጠው አገልግሎት መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎችን የያዘና ለአያያዝም ምቹና ቀላል በመሆኑ ምርትን በቀላሉ ለማስተዋወቅ ይረዳል፡፡

8) **ፖስተርና ባነር** የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፖስተርና ባነርን በመጠቀም የደንበኞችን ፈጣን ምላሽ ለማግኘት የሚያስችል የማስተዋወቂያ ዘዴ ነው፡፡ ፖስተርና ባነር በአነስተኛ ዋጋ የሚታተሙ በመሆናቸውና በተለያዩ ቀለሞች ደምቀው የሚዘጋጁ በመሆናቸው በቀላሉ የሚታዩና የተጠቃሚዎችን ቀልብ መሳብ ስለሚችሉ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ጉልህ ሚና





አላቸው፡፡ አንድ ጊዜ የተዘጋጁትን ፖስተርና ባነር በተለያዩ ጊዜያት መጠቀም ከማስቻሉም በላይ ፣ የድርጅቱን የምርት ዓይነቶች በሙሉ የሚያስተዋውቁ የተለያዩ ፖስተሮችንና ባነሮችን በአንድ ክፍል/ቦታ ማቅረብ ይቻላል፡፡

9) **ቢል-ቦርድ** በቋሚነት ምርትና አገልግሎትን የማስተዋወቂያ ዘዴ ነው፡፡ ቢል-ቦርድ ትኩረትን የሚስብና ራሱን የሚገልጽ፣ ትልቅና ሰፊ ገበያን ማዕከል ተደርጎ ስለሚዘጋጅ ብዙ ደንበኞችን በመሳብ የሽያጭ መጠንን ለመጨመር ያግዛል፤ በተጨማሪም የኢንተርፕራይዞችን ዝናና ታዋቂነት ለመገንባት አቅም ያለው የማስተዋወቅ ዘዴ ነው፡፡

10) **ጋዜጣ፣ መጽሔትና ብሮሸር** ተንቀሳቃሽና ለአንባቢያን ተደራሽ በመሆናቸው መረጃን ለመለዋወጥ አመች የማስተዋወቂያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ጋዜጣ፣ መጽሄትና ብሮሸር ስለምርቱና አገልግሎቱ ዝርዝር የሆኑ መረጃዎችን እንዲያካትቱ አድርጎ ለማዘጋጀት ስለሚያስችል የኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት ሙሉ መረጃ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ በመፍጠር ውጤታማ የማስተዋወቂያ መንገድ ነው፡፡

11) **ሬዲዮና ቴሌቪዥን** የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሬዲዮና ቴሌቪዥንን በመጠቀም ምርትና አገልግሎታቸውን ሲያስተዋውቁ ሰፊ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ በሬዲዮና ቴሌቪዥን የማስተዋወቅ ዘዴ ድምጽና ምስልን በመቀያየር ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ ስለሚያስችሉና የምርቱንና አገልግሎትን አጠቃቀም የሚገልጹ

በመሆናቸው ተጠቃሚዎችን በመቀስቀስ ኢንተርፕራይዙ በገበያ ውስጥ በሚኖረው ድርሻ ላይ ተጽዕኖ መፍጠር የሚያስችል የማስተዋወቂያ ዘዴ ነው።

12) በየክልሉ እና በፌዴራል የሚሰራጩ የመንግስት ሚዲያዎች ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎቶች በሕብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ልዩ ትኩረት ሰጥተው ድጋፍ ያደርጋሉ።

ሀ) የመንግሥት ሚዲያዎች የኢንተርፕራይዞችን አቅም ባገናዘበ መልኩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ለማስተዋወቅ የክልሉ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከክልሉ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት ለሀገር ልማትና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ያላቸውን አስተዋጽኦ ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል።

ለ) ኢንተርፕራይዞች ምርቶችንና አገልግሎቶችን በተለያየ መንገድ ለሕብረተሰቡ ያስተዋውቃሉ።

ሐ) በሀገር ውስጥ የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ትኩረት በመስጠት ለዝግጅቱ ልዩ የሚዲያ ሽፋን ይሰጣሉ።

13) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የገበያ ተወዳዳሪነትን ለማጠናከርና ለማሳደግ እንዲቻል የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያ በሚከተሉት የቴክኒክ ድጋፎች ዙሪያ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ይደረጋል።





ሀ) ስለምርት አስተሻሸግ ዘዴ፣ በገበያ ተወዳዳሪነት ስለሚኖረው ፋይዳ፣

ለ) በምርት አስተሻሸግ ፣ ይዘት ፣ አጠቃቀም የጥራት ደረጃ መግለጫ እና ሌሎች ከደንበኞች ፍላጎት ጋር የተቆራኙ መረጃዎችን ያካተተ የማስታወቂያ ስልቶችን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ይሰጣል፣

ሐ) ስለንግድ ስምና ምልክት አሰጣጥና ጠቀሜታ በገበያ ተወዳዳሪነት በምርት ማስተዋወቅ ያለውን የጎላ ፋይዳ በግልጽ እንዲገነዘቡ ድጋፍ ያደርጋል።

14) ኢንተርፕራይዞች ለምርቶቻቸው የጥራት ደረጃና ሰርተፊኬሽን እንዲኖራቸው በፈለጉ ጊዜ በከተሞች የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ አስተባባሪነት ከሚፈልጉት አካል የጥራት ደረጃና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረጋል።

15) መልካም ተሞክሮ እና የዳበረ ልምድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሀገር አቀፍ የምርት ጥራት ደረጃ ላይ ለደረሱና ስኬታማ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች በየዓመቱ እየተመረጡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የምርጥ ኢንተርፕራይዞች እውቅና ተሰጥቷቸው እንዲሸለሙ ይደረጋል።

# ክፍል አራት

## የፈጻሚ አካላት ሚና

### 16. የፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ሚና

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት ለመደገፍ በየደረጃው የተዋቀሩ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የገበያ ልማትና ግብይት ሥርዓትን ከማጠናከር አንጻር የሚከተሉት ድርሻዎች ይኖራቸዋል::

**1) ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር**

ሀ) በፌዴራል ደረጃ የሚደረጉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አጠቃላይ የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓት በመስክ ጉብኝት፣ ከየክልሉ በሚቀርቡ ሪፖርቶችና ኢንተርፕራይዞች ጋር በሚደረጉ ውይይቶች መሠረት በማድረግ በየሦስት ወሩ በሚካሄዱ የጋራ መድረኮች አፈፃፀሙን በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

ለ) በጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር በትልልቅ ፕሮጀክቶች በንዑስ ተቋራጭ እንዲተሳሰሩ ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴርና ሌሎች አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፤

ሐ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮችን መደገፍ::





**2) የንግድ ሚኒስቴር፤**

ሀ) በሚኒስቴር መስሪያቤቱ የሚወጡ ወይም የሚሻሻሉ የህግ ማእቀፎች የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ያማከለ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል::

ለ) የዘርፉን ልማት የሚጎዱ ህገወጥ የግብይት ተግባራትን መከታተል፣ መቆጣጠርና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ::

**3) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤**

ሀ) በአነስተኛ በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚፈለጉ የምርት ግብዓቶችን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ተቋራጭነት፣ በፍራንቻይዚንግ፣ አውትሶርሲንግና በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት እንዲተሳሰሩ ድጋፍ የማድረግ፤ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤

ለ) ሰፊ የኤክስፖርት ገበያ የሚያገኙ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በንኡስ ተቋራጭነት፣ በአውትሶርሲንግና በአውትግሮወር የግብይት ስርዓት እንዲተሳሰሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

**4) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር**

ሀ) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚወጡ ወይም የሚሻሻሉ የመንግስት ግዥ መመሪያ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ያማከለ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል::

ለ) በመንግስት የግዥ መመሪያ ሁሉም አስፈፃሚ አካላት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

ሐ) በመንግስት የግዥ መመሪያ የአፈጻጸም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

**5) የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር**

ሀ) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሽማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ተግባርና ሃላፊነት አንጻር የሚወጡ ወይም የሚሻሻሉ መመሪያዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የገበያ እድል የሚፈጥርና ተጠቃሚነት ያማከለ እንዲሆን ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡

ለ) በየአካባቢው የሚገኙ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ሱቆች ከተቋቋሙበት ዓላማ አንጻር ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

ሐ) የሸማቾች ህ/ስራ ማህበራት ሱቆች ለአካባቢው ህብረተሰብ የሚያቀርቡት የምርት አይነት እንዲጨምር፤ የሽያጭ መጠናቸው ከፍ እንዲልና ገቢያቸውም እንዲጨምር ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤በሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

መ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶችን በመረከብ ሊያስተዋውቁና ሊሸጡ የሚችሉ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራቶችን የመለየትና ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡





**6) የትምህርት ሚኒስቴር**

ሀ) ዩኒቨርሲቲዎች የልህቀት ማእከል ከመሆናቸው በተጨማሪ ሰፊ የገበያ እድል የሚፈጥሩ ስለሆነ በምሩቃንና በሌሎች ስራ ፈላጊ ወጣቶችና ሴቶች ለተቋቋሙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታና በነባር ዩኒቨርሲቲ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ውስጥ ከተቋራጮች ጋር በንኡስ ተቋራጭነት የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸው ወይም በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፡፡

ለ) በዩኒቨርሲቲዎች በዋናነት ከሚሰሩ የማስተማርና የምርምር ስራዎች በተጓዳኝ የሚሰሩ ስራዎች የምግብ አቅርቦት አገልግሎት፣ የካፍቴሪያ አገልግሎት፣ የፅህፈት አገልግሎት፣ የፎቶ ኮፒና የጥረዛ አገልግሎት፣ የጥበቃና ፅዳት አገልግሎት፣ የምድረግቢ ማስዋብ የመሳሰሉት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለተደራጁ ምሩቃን ወጣጦችና ሴቶች አውት ሶርስ በማድረግ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፡፡

**7) የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር**

በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክት በሚገኙ የገበያ እድሎች በምሩቃንና በሌሎች ስራ ፈላጊ ወጣቶችና ሴቶች ለተቋቋሙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከተቋራጮች ጋር በንኡስተቋራጭነት በማስተሳሰር ወይም በቀጥታ፣ በአዉትሶርሲንግና በአዉትግሮወር የግብይት ስርዓቶች የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ይደግፋል፣ ያስተባብራል፡፡

8) **የፌደራል የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ**

በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ገበያ ተኮር ስልጠናዎችና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ያስተባብራል:: ኢንተርፕራይዞች በገበያ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ:-

ሀ) በአካባቢ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ የገበያ እድሎች በሚወጡ ጨረታዎች ላይ የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ስለ ጨረታ ሰነድ ዝግጅት፣ የዋጋ አሞላልና የአቅርቦት ሁኔታ በቂ ድጋፍ እንዲገኙ ማድረግ፤

ለ) ስለምርት አስተሻሸግ ዘዴ፣ በገበያ ተወዳዳሪነት ስለሚኖረው ፋይዳ፣ በምርት አስተሻሸግ ይዘት፣ አጠቃቀም የጥራት ደረጃ መግለጫ እና ሌሎች ከደንበኞች ፍላጎት ጋር የተቆራኙ መረጃዎችን ያካተተ የማስታወቂያ ስልቶችን መሠረት ያደረገ ሥልጠና ይሰጣል፣

ሐ) ስለንግድ ስምና ምልክት አሰጣጥና ጠቀሜታ በገበያ ተወዳዳሪነት በምርት ማስተዋወቅ ያለውን የጎላ ፋይዳ በግልጽ እንዲገነዘቡ ድጋፍ ያደርጋል::

መ) ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ተክቶ በማምረት ሂደት በኢንተርፕራይዞች የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት ስልጠና ይሰጣል

9) **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በጨረታ በሚያሸንፉበት ወቅት በፋይናንስ እጠረት ምክንያት ያገኙትን የገበያ እድል እንዳያጡ የሚያስችሉ ድጋፎች በአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት እንዲመቻች ይደግፋል፣ ያስተባብራል:: ጨረታ ያሸነፉበትን ውል ታሳቢ በማድረግ የሶስትዮሽ ስምምነት በመፈፀም የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል::

10) **የፌዴራል ከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ**

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ከአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል::

ለ) እሴት ሰንሰለትን መሠረት በማድረግ በተለያዩ ክልሎች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለሀገር ውስጥ ገበያ በስፋት ሊመረቱ የሚችሉ ምርቶችን የገበያ ዕድል እና የሚያስፈልጉ ድጋፎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ዝርዝር የገበያ ፕሮፋይል ያዘጋጃል::

ሐ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ዘርፉን በየደረጃው የሚደግፉ አካላት የሚጠቀሙበትን በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋመውን ድህረ-ገጽ ያስተዳድራል::

መ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚዘጋጁ የንግድ ትርኢትና ባዛሮች የገበያ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል አገር አቀፍ ተሞክሮን መሠረት ያደረገ የንግድ ትርኢትና ባዛር አዘገጃጀት ስታንዳርድ ያወጣል::

ሰ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶችን ሀገር ውስጥ ገበያ እንዲያገኙ መከናወን ያለባቸውን ዝርዝር ተግባራት በመለየት የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ የማስተባበር ሥራ ያከናውናል፡፡

11) የክልል ከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

ሀ) በክልሉ ውስጥ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የገበያ ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት ለኢንተርፕራይዞች መረጃው እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

ለ) በክልል ውስጥ ከሚገኙ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በመቀናጀት በተለያዩ የግብይት ሥርዓቶችን በመጠቀም ከኢንተርፕራይዞች ጋር እንዲተሳሰሩ ያደርጋል፡፡

ሐ) በክልል ውስጥ ከሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ እንዲሁም የግሉ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የሚያገኙትን የገበያ ዕድል አሟጠው መጠቀም እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

መ) በከተማ የስራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽ/ቤትና በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚገኙ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስራ ያካሄዳል፡፡

ሠ) በየደረጃው ያሉ የኤጀንሲው ጽ/ቤቶች ጨረታውን ያሸነፈው ኢንተርፕራዝ/ዞች የተከፈላቸውን ቅድመ ክፍያ ለታቀደው ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፤





በየደረጃው ለሚገኘውና አንድ እርከን ከፍ ብሎ ላለው መዋቅር ይቀርባል፡፡ የሪፖርት፣ የመረጃ ልውውጥና አያያዙም ከማኑዋል አሰራር ወጥቶ በዘመናዊ በሆነ አሰራር ተደግፎ እንዲሰራና እንዲያዝ ይደረጋል፡፡ የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ይደረጋል፡፡

2) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ እድሎችን አሟጠው እንዲጠቀሙ በማስቻል ረገድ መመሪያው በየደረጃው ተግባራዊ መደረጉን፣ የተገኙ ስኬታማ አፈፃፀሞችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመስክ ክትትልና ድጋፍ ይረጋገጣል፡፡ የፌዴራል ኤጀንሲው፣ ክልሎች እና በየደረጃው የሚገኙ መዋቅሮች በተቀመጠው አግባብ የገበያ ትስስር ለኢንተርፕራይዞች መፈጠሩን በክትትልና ድጋፍ የሚያረጋግጡ ይሆናል፡፡ የመስክ ክትትልና ድጋፉን መነሻ በማድረግ ግብረመልስ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. **መመሪያ ስለማሻሻል**

ይህ ሞዴል መመሪያ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንዲሁም ከአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር ለማጣጣም መሰረታዊ ይዘቱን ሳይለቅ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ወይም በፌዴራል ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር አማካኝነት ሊሻሻል ይችላል።

19. **መመሪያው ስለሚጸናበት ሁኔታ**

ይህ ሞዴል መመሪያ ከፀደቀበት ከግንቦት 14 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ጃንጥራር አባይ**

**የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር**